ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies(FSS)

የፖሊሲ ፍሬ ኃሳቦች

ህዳር 2013 ቁጥር 40

# የገጠር መሬትና የምግብ ዋስትና በኢትዮጵያ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ ነክ ምርምሮችን የሚያካሂድ ለትርፍ ያልተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው።

♣ ♣ ♣

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሠብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል።

♣ ♣ ♣

በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፤ በልማት ዙሪያ ውይይቶችንም ያካሂዳል።

♣ ♣ ♣

በርዕሱ ዙሪያ ኃሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜል አድራሻችን ላኩልን።

♣ ♣ ♣

ኢሜል፡ fss@ethionet.et

ድረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org

## መግቢያ

በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ተሰማርተው ለሚገኙ ሰዎች መሬት እጅግ አስፈላጊ የተፈጥሮ ሀብት እና የመተዳደሪያ ምንጭ ነው። የአስፈላጊነቱን ደረጃ እንደየግለሰቦቹ እንደተሰማሩበት የስራ መስክ አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ ተብሎ ሊቀመጥ ይችላል። ግብርና፣ የደን ልማት፣ የማዕድን ልማት እና አሳ ማስገር በመሳሰሉ መተዳደሪያ መስኮች ለተሰማሩ መሬት በአንደኛ ደረጃ አስፈላጊ ግብዓት የሆነባቸው ሲሆኑ በእነዚህ ዘርፎች ያለመሬት አቅርቦት ስራዎቹ በፍፁም ሊከናወኑ የማይችሉ ናቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ እንደየአካባቢው የልማት ደረጃ የሚያስፈልገው የመሬት መጠን ይለያያል። ለምሳሌም ያህል በታዳጊ ክልሎች ያሉ ገበሬዎች አብዛኛውን ጊዜ ምርታማነታቸው አነስተኛ በመሆኑ የሚያስፈልጋቸውን የምርት መጠን ለማምረት ከሌላው በተለየ ሰፊ መሬት ያስፈልጋቸዋል።

ኢትዮጵያ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍሏ በመሬትና ከመሬት በሚገኙ ሀብቶች ላይ ጥገኛ የሆነ የግብርና ሀገር ነች። የሀገሪቷ ጠቅላላ የመሬት ስፋት አንድ ነጥብ አንድ (1.1)ሚሊዮን ካሬ ኪሎሜትር ሲሆን ከሀገሪቱ ህዝብ ሰማንያ በመቶ (80%) የሚሆነው በገጠሩ የሀገሪቱ ክፍል የሚኖርና ኑሮውም በግብርና(በሠብል ልማት እና በከብት እርባታ) ላይ የተመሠረተ ነው። በኢትዮጵያ ግብርና ሰላሳ ዘጠኝ በመቶ (39%) የሚሆነውን የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) እናሰማንያ በመቶ (80%) በመቶ የወጪ ንግድ ገቢ ይይዛል። አነስተኛ እርሻ መሬቶች ከጠቅላላው የእርሻ መሬት ዘጠና በመቶ (90%) የሚሆነውን የሚሸፍኑ ሲሆን፤ዘጠና አምስት በመቶ (95%) የሚሆነውን አጠቃላይ የግብርና ምርት በነዚሁ አነስተኛ የእርሻ መሬቶችና ገበሬዎች የሚሸፈን ነው። ከእነዚህ አኃዞች መሬት ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እና ለህዝቧ የምግብ ዋስትና ወሳኝ የሆነ ሀብት መሆኑን በግልፅ ያመለክታሉ።

መሬት ለምርት ወሳኝ ግብዓት ሲሆን ከመሬት ጋር የተያያዘ ማንኛውም ችግር የሀገሪቱን ህዝብ በተለይም ደግሞ የገጠሩን ማህበረሰብ መተዳደሪያ እና የምግብ ዋስትና በእጅጉ ይጎዳል። ከህዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ አንድ ቤተሰብ በነፍስወከፍ የሚይዘው የመሬት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ ሄዷል። በአሁኑ ጊዜ ነፍስ ወከፍ አማካይ የቤተሰብ የእርሻ መሬት መጠን 0.8 ሔክታር ሆኗል። መሬት ፈላጊ ወጣት የህብረተሰብ ክፍል እየጨመረ መሄዱን ተከትሎም የመሬት አልባው ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ ይገኛል። በአንዳንድ የገጠር ማህበረሰቦች መሬት አልባ የሆኑ ቤተሰቦች ቁጥር የአካባቢውን ነዋሪ ግማሽ ያህል መድረሱን አንዳንድ ጥናቶች ያመለክታሉ።

ከመሬት እጥረት ጋር በተያያዘም በማህበረሰብ ወይም በቤተሰብ አባላት መካከል ለረጅም ጊዜ ሲደረግ የቆየው የእርሻ መሬት መከፋፈል ያስከተለው የመሬት መበጣጠስ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል። አነስተኛ የእርሻ መሬት ባላቸው ዘንድ የተሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም ያለው አቅም አናሳ መሆን እንዲሁም ከእርሻ ውጪ ባሉ ገቢ በሚያስገኙ ዕድሎች ተጠቅሞ ውጤታማ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀምና ምርታማነትን ለማሻሻል ያለው ዕድል ውስን መሆን ያለውን ችግር አባብሶታል። በውጤቱም በአብዛኛው የገጠር ማህበረሰብ ዘንድ የቤተሰብ አባላትን በበቂ ሁኔታና በዘላቂነት ለመመገብ አለመቻል (የምግብ ዋስትናን አለማረጋገጥ) አሳሳቢ ፈተና ሆኗል።

በአለም ዓቀፍ ደረጃ ስምምነት የተደረሰበትና በሰፊው ጥቅም ላይ የዋለው የምግብ ዋስትና ትርጉም መሠረት “የምግብ ዋስትና ደህንነት አለ የሚባለው ሁሉም ሰው፤ በማንኛውም ጊዜ በቂ፤ ደህንነቱ የተጠበቀ እና የተመጣጠነ/አልሚ ምግብ ለማግኘት አካላዊና ኢኮኖሚ አቅም ሲኖረውና የሚፈለገውን የምግብ አይነት በማግኘት ጥሩ እና ጤናማ ህይወት መምራት ሲችል ነው“ ነው (FAO 1996)። የምግብ ዋስትና አራት ዋና ዋና ልኬቶች ያሉት ሲሆን፤ እነዚህም አቅርቦት (availability)፣ ተደራሽነት (access)፣አጠቃቀም (Utilization)እና በዘላቂነት ማግኘት መቻል (stability) ናቸው። አቅርቦት ስንል በቂና ጥራት ያለው ምግብን ከሀገር ውስጥ ወይም ከውጭ በሚገባ ምርት ማግኘትን ያመላክታል። ተደራሽነት ስንል ደግሞ በቂና የተመጣጠነ ምግብን ለማግኘት በቂ ሀብት ወይም መብት (entitlment) መኖሩን ያስረዳል። አጠቃቀም በቂ የሆነ ምግብ፣ ንፁሕ ውሀ፣ ንጽህና፣ የጤና እንክብካቤ፣የተሟላ የምግብ ደህንነት እና ፍላጎት ተሟልቶ መጠቀም ሲቻል ሲሆን፤ በዘላቂነት ማግኘት መቻል ሲባል

ደግሞ በቂ የሆነ ምግብን በሁሉም ጊዜ፣ ያለምንም መቋረጥ (በኢኮኖሚ ሆነ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ በሚመጣ ቀውስ)እና በመደበኛነት ማግኘት መቻል ማለት ነው።

የመሬት ይዞታ (ባለቤትነት) ከምግብ ዋስትና ጋር ያለውን ግንኙነት ለማስረዳት ሁለት አይነት አመለካከቶች (አስተሳሰቦች) አሉ። የመጀመሪያው መደበኛ ወይም ተለምዷዊ (conventional) የሚለው አስተሳሰብ ሲሆን፤ በዚህ አስተሳሰብ መሬት እና ምግብ ተነጣጥለው ሲታዩ አይገባም፤ ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነትም አላቸው ሲል በሁለቱ መካል ባለው ግኙነት ላይ አጽንዖት ይሰጣል። በዚህ መሠረት የመሬት አቅርቦት ከምግብ ምርት፣ ገቢ ከማግኘት እና ተመጣጣኝ ምግብ ከመመገብ ጋር ቀጥታ የሆነ ዝምድና አለው በሚለው ሀሳብ ላይ ያተኩራል። ሁለተኛው አስተሳሰብ ተለዋዋጭ ወይም ተቀያያሪ (recursive/ dynamic) የምግብ ዋስትና አስተሳሰብ የሚባለው ሲሆን ይህ አስተሳሰብ በመሬትና በምግብ መካል ያለውን ግንኙነት በዘላቂ መተዳደሪያ አቀራረብ መነጽር ይመለከታል። በዚህ አስተሳሰብ መሬትን በአንድ መልኩ ለምርት ግብዓት እንደሚውል የተፈጥሮ ሀብት ሲታሰብ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በሌሎች ሀብቶች (ለምሳሌምበገንዘብ፣ አካላዊ ሀብት (physical capital)፣ ማህበራዊ ሀብት)ሊቀየር እንደሚችል ሀብት ይወስዳል። ይህም ኢንቨስትመንትንና ተጠቃሚነትን ሊያስፋፋ እንደሚችል ያስረግጣል። ይህ የፖሊሲ ምክረ ሀሳብ በዋናነት መደበኛ (ተለምዷዊ) የሆነውን የመሬት እና ምግብ ግንኙነት ያገናዘበ ሲሆን የተቀያያሪ/ተለዋዋጭ ግንኙነትንም (dynamic linkege) አመለካከትን ለመዳሰስ ይሞክራል።

በአሁኑ ወቅት አንድ አራተኛ የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ በአሳሳቢ ሁኔታ የምግብ ዋስትና የሌለውና በቀንም ለሰው ልጅ ያስፈልገዋል ከሚባለው ዝቅተኛ ሁለት ሺህ አንድ መቶ (2100)ካሎሪ በታች የሚመገብ ነው። በዚህም ሀገሪቱ ከፍተኛ የሆነ የምግብ ዕጥረት ያለባት እንደሆነች ይታመናል። ከአምስት ዓመት በታች ከሆኑ ህፃናት መካከል አርባ በመቶ (40%) ያህሉ የቀነጨሩ ፤ ዘጠኝ በመቶ (9%) የሚሆኑት እጅግ በጣም የከሱ (wasted) ሀያ አምስት በመቶ (25%)የሚሆኑት በዕድሜአቸው ከሚጠበቀው ዝቅተኛ ክብደት በታች ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ ላለፉት ኃምሳ ዓመታት በአማካይ አራት ነጥብ አምስት (4.5) ሚሊዮን ሰዎች በየዓመቱ በምግብ ዕጥረት ቀውስ ይሰቃያሉ። በዓለም አቀፍ የረሀብ አመላካች ኢንዴክስ (global hunger index) ኢትዮጵያ ሀያ ስምንት ነጥብ ዘጠኝ (28.9) ነጥብ በማምጣት አገሪቱ ያለው የረሀብ እና የተመጣጠነ ምግብ ዕጥረት አሳሳቢ ከፍተኛ ተብሎ የተመደበ ነው።

በኢትዮጵያ ለሚታየው የምግብ ዋስትና አለመኖር የስነ ህይወት፤ ማህበራዊ፤ኢኮኖሚያዊ፤ እና የስነ-ህዝብ ምክንያቶች እንዲሁም የእነዚህ ምክንያቶች መስተጋብር አስተዋፅኦ አድርጓል። አብዛኛው አገሪቱ ህዝብ የሚኖረው በገጠሩ አካባቢ ከመሬት ጋር በቀጥታ በተገናኘ የኑሮ እንቅስቃሴ በመሆኑ እንደመሬት ዕጥረት እና መሬት አልባነት ያሉ ከመሬት ጋር የተያያዙ ችግሮች የገጠር ቤተሰቦችን የምግብ ዋስትና በእጅጉ ይፈታተናል።

የሁለተኛ ደረጃ መረጃን (desk review) በመመርመር ይህ የፖሊሲ ረቂቅ ሀሳብ የተፃፈበት ዋናው የምርምር ወረቀት በኢትዮጵያ በመሬት ዕጥረት/አልባነት እና በምግብ ዋስትና መካከል ያለውን ግንኙነት በስፋት ተመልክቷል። ለምግብ ዋስትና ችግር መፍትሔ የሚሆኑ የፖሊሲ ሀሳቦችን አመላክቷል ዋናው የጥናት ወረቀት በኢትዮጵያ አርሶ አደር እና አርብቶ አደር ማህበረሰቦች ላይ ቀድሞ በተሰራ ጥናት ላይ የተመረኮዘ ነው።

## ዋና ዋና ጉዳዮች፡- መሬት እና እርሻ

ኢትዮጵያ ኃምሳ አንድ ነጥብ ሶስት (51.3) ሚሊዮን ሔክታር የሚታረስ መሬት ቢኖራትም ለእርሻ የዋለው መሬት ከሀያ በመቶ (20%) በታች ነው። የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን (CSA) መረጃ እንደሚያሳየው የሚታረሰው መሬት መጠን እና የአርሶ አደሮች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። የሕዝብ ቁጥር መጨመር እንዲሁም ከእርሻ ስራ በመውጣት በሌላ የኢኮኖሚ ዘርፍ የሚሰማሩ ሰዎች ቁጥር ማነስ ለአርሶ አደሮች ቁጥር መጨመር ምክንያት ነው። አነስተኛ መሬት ያላቸው አርሶ አደሮች መሬታቸውን ለማስፋት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የግጦሽ መሬቶች፤ ደን አካባቢዎች እና ህዳግ መሬቶች (marginal lands) ወደ እርሻ መሬትነት በፍጥነት እየተቀየሩ መጥተዋል።

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በግብርና የሚተዳደሩ ቤተሰቦች ቁጥር ከአስራ አምስት (15) ሚሊዮን በላይ ሲሆን በሁሉም ዓይነት ሠብል የተሸፈነው እርሻ መሬት ከአስራ አራት (14) ሚሊዮን ሔክታር በላይ ነው። የማዕከላዊ ስታትስቲክ ኤጀንሲ በእርሻ መሬት መጠን ላይ ያደረገው አንድ ጥናት እንዳመለከተው አንድ ባለይዞታ በባለቤትነት የሚይዘው የመሬት ይዞታ መጠን ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ጀምሮ እየቀነሰ በመምጣት በ2010 ዓ.ም 0.8 ሔክታር ደርሷል። አገሪቱ በግብርና ምርት ረገድ ጥሩ አቅም ቢኖራትም ላለፉት አስርት ዓመታት የምግብ ዋስትና ዕጥረት በቋሚነት የሚታይባት አገር ሆናለች።

## የምግብ ዋስትና

በኢትዮጵያ ላለው የምግብ ዋስትና ችግር መንስኤዎቹ በርካታና ውስብስብ ናቸው። ስነ ህይወታዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ስነ ህዝባዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና የመሠረተ-ልማት ችግሮች በምግብ አቅርቦት፣ ተደራሽነት እና አመጋገብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራሉ። ለምግብ ዋስትና አለመኖር ዋና ዋና መንስኤዎች ተብለው ከተዘረዘሩት መካከል ድርቅ፣ የጎርፍ መጥለቅለቅ፣ የመሬት መሸርሸር፣ ድህነት እና ደካማ የጤንነት ሁኔታ፣ ፈጣን የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ ግጭቶች እና የመልካም አስተዳደር እጦት በዋናነት ይጠቀሳሉ። አስከፊ ከሆኑ የረሀብ ገፅታዎች መገንዘብ እንደሚቻለው ድርቅ በምግብ ዕጥረት ላይ አደጋን ከሚያስትሉ ችግሮች ዋነኛው ነው። በኢትዮጵያም ለምግብ ዕጥረት ዋነኛ ከሆኑ ምክንያቶች አንዱ የድርቅ አደጋ ነው።

ጎርፍ በዋናነት ወንዞች በሚያልፉባቸው ሜዳማ ቦታዎች ላይ በስፋት ይከሰታል። ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ ከሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ድሆች፣ ህፃናት ፣ አዛውንቶች፣ የሚያጠቡ እና ነፍሰጡር እናቶች ዋነኞቹ ናቸው። የደን መጨፍጨፍ የአፈር መሸርሸርን በማስከተል የምግብ ዋስትና ዕጦትን ያስከትላል፤ ያባብሳል። በዓለም የምግብ ድርጅት (FAO፣ 1986) የተጠና አንድ ጥናት እንደሚያመለክተው በየዓመቱ ከእያንዳንዱ ሔክታር መሬት ላይ አንድ መቶ ቶን አፈር በመሸርሸር ይጠፋል። ከአስርት ዓመታት በፊትም አርባ በመቶ (40%) የነበረው የአገሪቱ የደን ሽፋን ተመናምኖ አሁን ወቅት ከአስራ አምስት በመቶ (15%) በታች ሆኗል። ይህ የደን ሽፋን መቀነስና የመሬት መሸርሸር ምርታማነትን ከመቀነሱም ባሻገር ሀገሪቱ ከግብርና የምታገኘውን የሀገር ውስጥ ምርት በሦስት በመቶ (3%) እንዲቀንስ አድርጓል።

በኢትዮጵያ ላለው የምግብ ዋስትና ችግር ድህነት እንደዋነኛ ሌላ ምክንያት ይጠቀሳል። በአሁኑ ወቅት ሀያ

አምስት በመቶ (25%) የሚሆነው የሀገሪቱ ህዝብ ከድህነት ወለል በታች ይኖራል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ኢትዮጵያ በሰው ልማት አመላካች ዋጋ (Human Development Index) 0.489 ነጥብ ያላት ሲሆን፤ ከአንድ መቶ ሰማያ ዘጠኝ አገሮች አንድ መቶ ሰባ ሦስተኛ ደረጃ ትገኛለች፡፡ ድሆች እና እጅግ ችግረኛ (destitute) ሰዎች ለምግብ ዕጥረት ተጋላጭ መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ ከፍተኛ የሆነው በአማካይ ሁለት ነጥብ አምስት በመቶ የሚያድገው የህዝብ ቁጥር ለምግብ አቅርቦትም ሆነ ተደራሽነት ችግር ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያለው አሳሳቢ የመሬት ዕጥረት ችግር (በአማካይ በቤተሰብ 0.8 ሔክታር) እና በከተሞች የሚታየው ከፍተኛ የሆነ የስራ አጥነት ችግር ከህዝብ ቁጥር መጨመር ጋር የተያያዙ መዘዞች ናቸው፡፡ ለዓመታት የዘለቀው ግጭትና የሰላም መደፍረስም በኢትዮጵያ ላለው የምግብ ዋስትና ችግር የራሱ ድርሻ አለው፡፡ ውድና ጥቂት በሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ያለ ሽሚያ፣የመሬትና የባለቤትነት መብቶች ችግር፣ ችግሮቹን የሚመጥኑ የፖሊሲ ምላሾች አለመኖርና ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ እንቅስቃሴዎች በሀገሪቱ ለሚታዩት ግጭቶች ዋና ዋና መንስኤ የሚባሉት መካከል መጥቀስ ይቻላል፡፡ የምግብ ዋስትናን አደጋ ላይ የሚጥሉ ከመልካም አስተዳደርና ፖሊሲዎች ጋር የሚያያዙ ተግዳሮቶች የመልካም አስተዳደር ዕጦት ፣ ደህን ያማከለ ፖሊሲ አለመኖር እና በቂና አስተማማኝ የሆነ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት አለመኖሩ ሌሎች የምግብ ዋስትና ችግርን ያባባሱ ምክንያቶች ተደርገው ይጠቀሳሉ፡፡

በመሬት እና ምግብ ዋስትና መካከል ያለ ግንኙነት

በገጠር ኢትዮጵያ የተሰሩ በርካታ ምርምሮች የምግብ ዋስትና ከመሬት ይዞታ መጠን ጋር አዎንታዊ ግንኙነት እንዳላቸው ያመለክታሉ፡፡ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ በሙኔሳ ወረዳ የሚገኙ ሦስት ማህበረሰቦች ውስጥ የተደረገ አንድ ጥናት መሬት አልባ የሆኑ ቤተሰቦችለምግብ ዕጥረት በከፍተኛ ሁኔታ የተጋለጡ እንደሆኑበዝርዝር አመላክቷል፡፡ በመሬት አልባነትና በምግብ ዕጥረት መካከል ያለውንም ግንኙነት ሲያስረዳ፡

"በመጀመሪያ መሬት አልባ እና በቂ መሬት የሌላቸው ደሀ ቤተሰቦች መተዳደሪያቸውን ለማግኘት መሬት ይከራያሉ ወይም በጋራ ያርሳሉ፡፡ በጋራ እርሻ የመሬቱ ባለቤቶች ከሚገኘው ምርት በዓይነትና በገንዘብ ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ ይህ ድርሻ እስከ ኃምሳ በመቶ ሊደርስ ይችላል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የማህበረሰቡ አባላት መሬት አልባነት ወይም በቂ መሬት አለመኖር ማህበራዊ አለመረጋጋትን እንዳስከተለ ያምናሉ፡፡ በዚህም አንዳንድ መሬት አልባ ሰዎች በመተዳደሪያ ዕጦት ሳቢያ እንደ ስርቆት እና ዘረፋ ያሉ አላስፈላጊ ተግባራት ላይ መሳተፋቸውን እንደምክንያት ያነሳሉ፡፡ በሦስተኝነት ከእርሻ ውጪ የሆኑ ገቢ የማግኛ የስራ ዕድሎች አለመኖር ከፍተኛ ከሆነው የህዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ተዳብሎ የምግብ ዕጥረቱን ችግር አባብሶታል፡፡ ይህም የሆነው የሁሉም ገጠር ነዋሪ ትኩረት በተለመደው የገጠር ኑሮ ምንጮች ላይ ማለትም በሠብል ምርት እና ከብት ዕርባታ ላይ ብቻ በመሆኑ ነው፡፡ በአራተኛ ደረጃ በተለያዩመሬት ማግኛ መንገዶች መሬት አልባ ቤተሰቦች መሬት ማግኘት የሚችሉት ለአንድ ወቅት ብቻ ከመሆኑ ባሻገር በመሬቱ ላይ የይዞታ ባለቤትነት መብት የላቸውም፡፡

በሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ የተጠና ሌላ ጥናት በመሬት እና የምግብ ዋስትና መካከል ተመሳሳይ ግንኙነቶችን አመልክቷል፡፡ ይኸውም መሬት አልባ ወይም በቂ መሬት የሌላቸው ገበሬዎች በአንፃራዊ ሁኔታ በቂ መሬት ካላቸው አቻዎቻቸው ጋር ሲነፃፀር የሚመገቡትን በቂ ምግብ ለማምረት ያላቸው አቅም ውሱን ነው (Degefa 2003)፡፡ ጥናቱም ‹ደሀ› እና ‹እጅግ በጣም ደሀ› የተባሉት መሬት አልባ ወይም በቂ መሬት የሌላቸው ቤተሰቦች በአብዛኛው ለምግብ ዕጥረት ቀውሶች የሚጋለጡ እንደሆኑ አመልክቷል፡፡

በኦሮሚያ፣ በአማራ እና ደቡብ ክልሎች ባሉ ስድስት ወረዳዎች (እያንዳንዱ ሁለት ወረዳዎች) የተካሄደ ጥናት የመሬት ይዞታ መጠን መጨመር ከምግብ ዋስትና ሁኔታ መሻሻል ጋር እንደሚያያዝ አሳይቷል፡፡ ከአንድ ሔክታር በታች መሬት ካላቸው ቤተሰቦች ጋር ሲነፃፀር ከአንድ እስከ ሁለት ሔክታር መሬት ያላቸው ቤተሰቦች ኃምሳ ዘጠኝ በመቶ ያህል የተሻለ የምግብ ዋስትና አላቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከሁለት ሔክታር በላይ ያላቸው ቤተሰቦች 1.34 ዕጥፍ የምግብ ዋስትናቸው የተረጋገጠ ነው፡፡

አነስተኛ የመሬት ይዞታ መጠን የምግብ ዋስትና አለመኖርን በሁለት መንገድ እንዲከሰት ያደርጋል፡፡ በመጀመሪያ አነስተኛ የእርሻ መጠን ያላቸው ቤተሰቦች ብዙ ጊዜ ድሆች በመሆናቸው እና ትርፍ ምርት ስለማይኖራቸው የግብርና ቴክኖሎጂዎችንና ሌሎች ግብዓቶችን ለመግዛት አይችሉም፡፡ በሁለተኛ ደረጃ እነዚህ ገበሬዎች መሬትን ለመንከባከብ ያላቸው ፍላጎት በሁለት ምክንያት የተገደበ ነው፡፡ መሬታቸው አነስተኛ መጠን ያለው በመሆኑ ባህላዊ የሆነው የመሬት አጠባበቅ ልምድ መሬትን ማሳረፍ (fallowing) አይችሉም፡፡ እንደ ሰብል ቅሪት እና እንስሳት ፍግ የመሳሰሉትን ተረፈ ምርቶችን ለአፈር ጥበቃና ምርታማነት ማሳደግ ከመጠቀም ይልቅ በመሸጥና ገቢን በማግኘት ያላቸውን ክፍተት ይሞላሉ (Degefa etal 2017)፡፡ በጥናቱ የተካተቱ ቤተሰቦች መካከል ሁለቱ የመሬት ዕጥረት እና መሬት አልባነት ኑሮአቸውን ምን ያህል አስቸጋሪ እንዳደረገውና ዘላቂ ለሆነ ለምግብ ዋስትና ዕጦት እንዴት እንዳጋለጣቸው አስረድተዋል፡፡

ሀ) በመሬት እጥረት ምክንያት የምግብ ዋስትና ችግር የገጠመው ቤተሰብ

ስሜ አጸደ ይባላል፡፡ በሀያ አመቴ አግብቼ የፈታሁና የአንድ ወንድ እና አንድ ሴት ልጆች እናት ነኝ፡፡ መሬት በሚከፋፈልበት ጊዜ ያገኘሁት ግማሽ ሔክታር መሬት አለኝ፡፡ የመጀመሪያ ባለቤቴ መሬት አለው፤ ነገር ግን መሬቱአነስተኛ በመሆኑ በፍቺ ጊዜ መሬት ለመካፈል ጥያቄ አላቀረብኩም፡፡ ሁለተኛው ባለቤቴንም ቢሆን መሬት እንዲያካፍለኝ አልጠየቅኩትም፡፡ እኔ የራሴ አነስተኛ መሬት ያለኝ ሲሆን በሬ የለኝም፡፡ በመሆኑም በጋራ ለማረስ ተገድጃለሁ፡፡ በቅርብ በነበረው የመኸር ወቅት በጋራ አርሰን ካገኘነው ሦስት መቶ ኪሎ አተር ምርት ውስጥ እኔ ያገኘሁት 150 ኪ.ግ ብቻ ነው፡፡ ይህ ፍላጎታችንን ለመሸፈን በቂ አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት በትንሽ መሬት ህይወትን መግፋት አስቸጋሪ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ በዚህም ሳቢያ ዕኩል ለመስጠት ተገድጃለሁ፡፡

በደቡብ ክልል ወናጎ ወረዳ ያሉ ገጠራማ አካባቢዎች ከመሬት ጋር ያልተያያዙ አማራጭ የኑሮ ዘይቤዎች (የመተዳደሪያም ምንጮች) ስለሌሉ መሬት አልባነት የምግብ ዋስትና ዕጥረትን ያስከትላል፡፡ ቀጥሎ ያለው መሬት አልባ ቤተሰብ ታሪክ በመሬት አለመኖር ምክንያት የኑሮ ደህንነታቸውና የምግብ ዋስትናቸው ምን ያህል እንደተፈተነ ያሳያል፡፡

ለ) በመሬት እጦት ምክንያት የምግብ ዋስትና ችግር የገጠመው ቤተሰብ

ስሜ ድባቤ ሲሆን 60 ዓመቴ ነው። የአራት ልጆች (3 ወንድ እና 1 ሴት) እናት ነኝ። የእርሻ መሬት የለኝም። ባለቤቴ ከ35 ዓመት በፊት በሞት ተለይቶኛል። አንድ ሔክታር መሬት ነበረን፤ ይኸም ለሁለት ወንድ ልጆቻችን ተሰጠ። ኑሯችን በዋናነት በሴፍቲ ኔት ላይ የተመሠረተ ነው። የምናገኘው ድጋፍ በዓመት የስድስት ወር ገንዘብና እህል ድጋፍ ነው። በቀሩት ወራቶች ቡና በመሰብሰብ የቀን ስራ ላይ እሳተፋለሁ። በመኖሪያ ቤቴ አካባቢ ጥቂት የቡና ዛፎችና የእንሰት ተክል አሉኝ። እህልም እገበያይ ነበር። ዕድሜዬ ገፍቷል፤ ነገር ግን ልጆቼን ለማብላት መስራት አለብኝ። የጤንነት ችግር ቢኖርብኝም የልጆቼን የኑሮ ፍላጎት ለሟሟላት የበለጠ መስራት አለብኝ። የምናገኘው ድጋፍቢኖርም እንኳን ዓመቱን ሙሉ የምግብ ዕጥረት አለብኝ። በበጋ ወቅት የምግብ ዕጥረቱ ይባባሳል። ችግሩን ለመቋቋም ቤታችን የሚገኘውን እንሰትና ጎመን እንጠቀማለን። በተጨማሪም ገንዘብ እና እንሰት እንበደራለን። የተበደርኩትን ገንዘብ ከከፍተኛ የወለድ ጋር እንመልሳለን። ገንዘቡን መመለስ እጅግ ከባድ ነው። አሁን በጣም ተስፋ ቆርጫለሁ፤ ልጆቹም የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም።

የፎርም ፎረ ሶሻል ስተዲስ በኢትዮጵያ አራት ዋና ክልሎች (በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ ደቡብ እና ትግራይ) በመሬት፣ መሬት አልባነት እና ድህነት ላይ ያተኮረ ጥናት አካሂዷል። የምርምሩ ግኝቶች እንደሚያመለክተው የመሬት አልባዎች ቁጥር በሁሉም ክልሎች እየጨመረ ሲሆን፤በዋናነት የህዝብ ቁጥር መጨመር ዋነኛው የመሬት አልባነት መስፋፋት ምክንያት መሆኑንም አሳይቷል። በጥናቱ በተካተቱት አራቱም ክልሎች የመሬት ዕጥረትና መሬት አልባነት በገጠር የወጣቶች ስራ አጥነትን፣ የተስፋፋ ድህነትንና ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግርን አስከትሏል።

የግጦሽ መሬት እያነሰ መምጣትና የውሀ ዕጥረት በአርብቶ አደር ማህበረሰብ አኗኗርና የምግብ ዋስትና ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። በቅርብ ጊዜ በደቡብ ኢትዮጵያ በቦረና አርብቶ አደሮች አካባቢ የተደረገ የመስክ ጥናት ይህንን ያረጋግጣል። ቦረና የወተት እና ወተት ተዋፅኦ እንዲሁም የጥራጥሬዎች ዕጥረት ያለበት አካባቢ እንደሆነም ተስተውሏል። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣው የምግብ አቅርቦትም ሆነ ተደራሽነት ችግር በብዙሀኑ ህዝብ ዘንድ የምግብ ዕጥረት አስከትሏል (Degefa 2018)። የበርሀማነት መስፋፋት፣ የግጦሽ መሬት በመጠን እና በጥራት መቀነስ፣ ድርቅና የአየር ንብረት መለዋወጥ፣የእንስሳት በሽታ፣የሰውና የእንስሳት ቁጥር መጨመር እንዲሁም ከግብይት ጋር የተያያዙ ችግሮች የእንስሳት ኢኮኖሚ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀዘቀዘ እንዲሄድ አስገድደውታል። የሰብል ምርት የጀመሩና ወደ ከፊል አርብቶ አደርነት ለመቀየር የሚሞክሩትም ቢሆኑ እንደ ድርቅ፣ወቅቱን ያልጠበቀ የዝናብ ሁኔታ፣ የአፈር ለምነት ማነስ እና ምርታማነት ማነስ ያሉ ችግሮች አጋጥሟቸዋል። ምንም እንኳን ደረቅማና ከፊል ደረቃማ በሆኑ የአርብቶ አደር አካባቢዎች የጋራ ይዞታዎች በስፋት ቢኖሩም በመሬት መጠን ስፋት እና በምግብ ዋስትና መካከል ያለውን ቀጥተኛ ግንኙነት ጥናቱ አመላክቷል።

ማጠቃለያ ሀሳቦች

በመሬትና እና በምግብ ዋስትና መካከል ካለው ትስስር አንፃር አንድ ሀገር የዜጎችን የምግብ ዋስትና እንዴት ማሻሻል እንዳለባት አንዳንድ አስተያየቶች መሰንዘር አስፈላጊ ነው። ኢትዮጵያ በድርቅ፣ በጎርፍ፣ የመሬት መሸርሸር፣ ድህነት፣ ፈጣን የህዝብ ቁጥር ዕድገት፣ ግጭት እና በመልካም አስተዳደር ዕጦት ሳቢያ የተከሰተባትንየምግብ ዕጥረት ችግሮችን ማስወገድ ስለምትችልባቸው መንገዶች በርካታ ጥናታዊ ፅሁፎች ተጽፈዋል። ይህ የፖሊሲ ምክረሀሳብ በቂ የሆነ መሬት ማግኘት መቻል የአርሶ አደሩንም የአርብቶ አደሩን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ወሳኝ እንደሆነ ያስረግጣል። ሆኖም ግን በከፍተኛ መጠን እየጨመረ ያለውን የሕዝብ ብዛትና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚታየውን ከፍተኛ የመሬት ፍላጎት መኖር ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ችግርን በዘላዊነት ለመፍታት መሠረታዊ የሆነ የኢኮኖሚ መዋቅር ለውጥ እንደሚያስፈልጋት አበክሮ ያስረዳል። ሀገሪቱ ኢኮኖሚዋን ከግብርና መርህ ወደ ኢንዱስትሪ መርህ ለመለወጥ በተጠናከረ መልኩ መስራት ይገባታል።

ደገፋ ቶሎሳ (ፕሮፌሰር)

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጂኦግራፊ እና የልማት ጥናት
ፕሮፌሰር እንዲሁም በሰላም ሚኒስቴር የፌደራሊዝም እና
የልዩ ድጋፍ ዳይሬክተር ጀነራል።

ምንጭ፡- ደገፋ ቶሎሳ (2013) የገጠር መሬትና የምግብ ዋስትና በኢትዮጵያ

ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ የፖሊሲ ፍሬ ሀሳብ የታተመው የኦፕን ሶሳይቲ ኢኒሼቲቭ ፎር ኢስተርን አፍሪካ (Open Society Initiative for Eastern Africa) የገንዘብ ድጋፍ ነው በዚህ ህትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሥራ አመራር ቦርዱን፣የድርጅቱን አጋሮችና የገንዘብ ድጋፍ የሠጠውን የኦፕን ሶሳይቲ ኢኒሼቲቭ ፎር ኢስተርን አፍሪካ (Open Society Initiative for Eastern Africa) አቋምና አመለካከት ላያንጸባርቅ ይችላል።

አድራሻ፡- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS) ፖ.ሣ.ቁ.፡- 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ፡- 011154 56 05/06 ፋክስ፡- 011154 56 07 ኢሜል፡- fss@ethionet.et ድረ-ገጽ:- www.fssethiopia.org